101



በሌላ በኩል ገን በሌሉበት ጉዳያቸው ሲታይ የቆዩትን ተከሣሾች አስመልክቶ ይህ ክስ ከቀረበ በኋላ እንዲቀርቡ ታዞ በአድራሻቸው ተፈልገው ባለመገኘታቸውና በማስታወቂያም ጥሪ ባለመቅረ,ቸው እስከአሁን እነሱ በሌሉበት ክርክሩ ቀጥሎ ሲታይ ቆይቷል::___

ስለዚህ፣ ክስ ቀርቦባቸው በማስረጃ ከተረጋገጠባቸው በኋላ ባለመኖራቸው ምክንያት የመከላከል መብታቸውን ተጠቀመው መከላከል ባለመቻላቸው በወ/መ/ሕ/ቁ/32//1/ሀ/ለ/ 281/ሀ/ ሥር ለዚህ ወንጀል ድርጊት ኃላፊና ተጠያቂ ከመሆን የሚያድናቸው ምክንያት ባለመኖሩ ጥፋተኞች ናቸው በለን የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተንባቸዋል::___

እንዲሁም 5ኛው ተከሣሽም በተጠቀሰው የወ/መ/ሕ/ቁ/522/1/ሀ/ሥር ለድርጊት 3 ወንጀል ጥፋተኛ ነው በለናል::ከዚህ በኋላ ዐ/ሕጉ ያላቸውን የቅጣት ሀሣብ እንዲሰጡ ተጠይቀ በእነዚህ ተከሣሾች ላይ የሚቀርበዉ ሪከርድ ባይኖርም ይህን ገዘፍ ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ ከሕግ ጥላ ሥር ለማምለጥ ተሰውሮ የጠፉ በመሆናቸውን የድርጊታቸውም ሁኔታ በቀላሉ የማታይ ስላልሆነ ከድርጊታቸው ጋር የሚመጥን ቅጣት ይወሰንባቸው በለዋል::

ይህ ፍ/ቤትም ከዐ/ሕጉ የቀረበውን የቅጣት አስተያየትና የሕጉን አላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀጥሎ ያለውን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተዋል::___

218

**<u>የ ቅ ጣ ት ው ሣ ኔ፣</u>**

እነዚህ ተከሣሾች የተከሰሱበት ወንጀል መፈጸማቸው ስለተረጋገጠባቸው ጥፋተኞች ናቸው ተብለዋል::እነሱ ስለሌሉ የቅጣት ሃሣባቸውን መስጠት ባይችሉም የወንጀሉን ድርጊት በሚፈጸሙበት ጊዜ የነበረውን የወቅቱን ሁኔታ ስናገናዝብ የፈጸሙት የወንጀል ድርጊት አሣዛኝ ቢሆንም በዚያን ጊዜ የነበረው የዘመነ መንግሥት ሥርዓትና ፖሊሲ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ለመፈጸም የሚጋብዝ እንደነበር የሕጉም አላማ አጥፊውን ቀጥቶ ለመቀበል ሣይሆን አስተምሮ ለመመለስ በመሆኑ ለፈጸሙት ድርጊት ትምህርት ለሌላም ጥንቃቄ እንዲሆን ሁኔታውን ከግምት ውስጥ በማስገባት 1ኛው ተከሣሽ አበራ ጉበና እጅ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በ12 አመት ጽኑ እስራት ፣ 3ኛው ተከሣሽ በዙ ወርቁ ዘውዱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በ15/አሥራ አምስት/ አመት ፀኑ እስራት እንዲቀጡ፣ 4ኛው ተከሣሽ ዘገሪያስ ኃይሉ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአሥራ አምስት/15/አመት ፀኑ እስራት እንዲቀጡ ፣ 5ኛው ተከሣሽ ሻ/ባሻ ደንደና ሠፈራ በዕድሜ ልክ ፀኑ እስራት እንዲቀጡ ፣ 10ኛው ተከሣሽ ዱኖስ ባሣሁን በ8/ስምንት/ አመት ፀኑ እስራት ፣ 16ኛው ተከሣሽ በቀለ ገለታም በ8 /ስምንት/

..../21

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa
ጠቅላይ ፍ/ቤት

102



18ኛ ተከሣሽ ጁሩታ ነገያ በ8/ስምንት/አመት ፅኑ እሥራት፣ 20ኛው ተከሣሽ ብያና ገለታ በ8/ስምንት አመት ፅኑ እሥራት ፣ ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ እንዲቀጡ ብለን ወስነናል፡፡___

ት ዕ ዛ ዝ ፣

እነዚህ ተከሣሾች በሰለባት ውሣኔ የተሰጠባቸው በመሆኑ በፖሊስ ታድኖ በተገኙበት ተይዘው የተፈረደባቸውን እሥራት ለመፈጸም እንዲችሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የፖሊስ ከፍለና ወህኒ ቤት ይጻፍ ብለናል፡፡ከዚህ በኋላ እንዲከላከሉ የተባሉት ተከሣሾች ፣

1. 2ኛው ተከሣሽ አብዲሣ ዶኑ ፣
2. 6ኛው ተከሣሽ የ10/አ/ተሾመ ገመዳ፣
3. 7ኛው ተከሣሽ ቡሌ ፈይሣ ፣
4ኛ. 8ኛው ተከሣሽ ሀብን አብዲ፣
5ኛ. 9ኛው ተከሣሽ በንቲ ኩሉ
6ኛ. 11ኛው ተከሣሽ ደ/ረዳሲ ገምታ፣
7ኛ. 12ኛው ተከሣሽ ደበሌ ዳባ፣
8ኛ. 13ኛው ተከሣሽ ደ/ር ፍያኑ ቶና
9ኛ. 14ኛው ተከሣሽ እንዳለ ኢተፋ
10ኛ. 15ኛው ተከሣሽ ተስፋዬ ተፈራ
11ኛ. 17ኛው ተከሣሽ ዐርጌ ጉተታ
12ኛው 19ኛው ተከሣሽ ጫንስ በለጠ
13ኛ.21ኛው ተከሣሽ አበማ ዑማ
14ኛ.23ኛው ተከሣሽ ተስፋዬ በር ሃኑ
15ኛ.24ኛው ተከሣሽ ሙሳጠፋ አብዲሣ
16ኛ. 26ኛው ተከሣሽ በቀለ ገመዳ እንዲከላከሉ በይኑ ከተነገራቸው በኋላ ሁሉቻው የመከላከያ ማስረጃ እንደሌላቸው እና ማቅረብ እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡ በ16/9/939// በማገላቸው በጽሬት ማመለከቻ ገለጸው ውሣኔ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡___

ስለዚህ፣ እነዚህ ተከሣሾች በለቀ ዐ/ሕጉ ክስ መሠረት የተከሰሰበት ወንጀል መፈጸማቸው በዐ/ሕጉ ማስረጃ በሚገባ ተረጋገጠባቸው እነሱም በበኩላቸው የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ቢነገራቸውም በዚህ ወብት ተጠቀመው የመከላከያ ማስረጃቸውን ለማቅረብ ባለመፈለጋቸው ወይም ባለመቻላቸው እና ለዚህ ለፈጸሙት ወንጀል ከተጠያቂነት የሚድኑበት መንገድ የለም ብለናል፡፡___

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa

219

- በመሆኑም 6ኛው ተከሣሽ የ10 አለቃ ተሾመ ጉደና በአንደኛ እና 35 የወ ንጀል ድርጊት በወ/መ/ሕ/ቁ/281/ሀ/ እና 522/1/_ሀ_ ሥር ለዚሁ ወንጀል ኃላፊና ተመደቂ ነው በለን የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተንበታል::

- እንዲሁም 8ኛው ተከሣሽ ሀሰን አበጊሣ በአንደኛ እና በ2ኛው ድርጊት በወ/መ/ሕ/ቁ/281/ሀ/ሥር ጥፋተኛ ነው በለን የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተናል::_

ሌሎች የተቀሩት ተከሣሾች ማለትም 2ኛ ፣ 7ኛ ፣ 9ኛ ፣ 11ኛ ፣ 12ኛ ፣ 13ኛ ፣ 14ኛ ፣ 15ኛ ፣ 17ኛ ፣ 19ኛ ፣ 21ኛ ፣ 23ኛ ፣ 24ኛ ፣ እና 26ኛ ተከሣሾች በተከሰሱበት ወንጀል አንዱ ድርጊት በወ/መ/ሕ/ቁ/281/ሀ/ሥር ጥፋተኞች ናቸው በለን የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተንባቸዋል::___

ከዚህ በኋላ ዐ/ሕጉ ስለቅጣት ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀ ተከሣሾች በተጠቀሰባቸው የሕግ አንቀጾች ሥር ጥፋተኞች መሆናቸው የተረጋገጠባቸው በመሆኑ ለጊዜው የማቀርባቸው ሪከርድ ባይኖርም በተለይ 6ኛው እና 8ኛው ተከሣሽ በሰብዓዊ ፍጥረት ላይ ሆን ብለው አስቀድሞ በማሰብ ጨካኝና አደገኛነታቸውን በሚገልጽ ሁኔታ ይህን ድርጊት በመፈጸማቸው ፍ/ቤቱ ከፍተኛውን ቅጣት እንዲወስንባቸው ሌሎች ተከሣሾችም ለሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ራሣቸውን በኮሚቴ አዋቅረው 8ት ተማሪዎች እንዲረሸኑ ወስነው ስለአስገ ደሉዋቸው ለወንጀሉ ባላቸው ተሣትፎ መጠን ለድርጊታቸው ተገቢ የሆነ ቅጣት እንዲወሰንባ ቸው አጠይቃለሁ ብለዋል::___

6ኛ ፣ 17ኛ ፣ 21ኛ ፣ እና 26ኛ ተከሣሾች ፍ/ቤቱ ባቈላቸው መበያ አማካኝነት 6ኛው ተከሣሽ ሥራው ሹፌር ስለነበረ በወቅቱ የታዘዘውን ሥራ ከመሥራት በስ ተቀር በራሱ ወሣኝነት የፈጸመው ተግባር አለመኖሩን ከዚህ ሌላ ሪከርድ ያልቀረበበት በመሆኑና የብዙ ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ ይህ ሁኔታ ታውቆለት ቅጣት እንዲቀለለት 17ኛ፣ 21ኛ ፣ 26ኛ ተከሣሾች ይህ ወንጀል በተፈጸመበት ወቅት ከመምህራን የተማሪ ዎች ኮሚቴ ተወካይ ሆነው መሥራታቸው ቢታወቅም በዚያን ወቅት በቂ የሕግ ግንዛቤ ስላል ነበራቸው እና ባለማወቅ የተሣተፉ መሆናቸውን ዶኔ እድሜአቸውም በአፍላ የወጣትነት ሁኔታ ላይ ስለነበሩ በሌላ መሠረት አንጂ ሌላ ግንዛቤ እንደሌላቸው በመታሰራቸው ምክንያት አሁን ቤተሰቦቻቸው ስለተበተኑ ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች [illegible] አስገብቶላቸው ቅጣቱን እንዲያቀልላቸው ጠይቀዋል::___

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa
Mana murtii Waliigala ... Supreme Court of Oromiya

_የግል ተከራካሪ 2ኛው ተከሣሽም ዕድሜ 73 ዓመት የሚለው በደም ብዛት በሽታ እየተ ሰቃዩ መሆኑን የትምህርት ደረጃው አነስተኛ እንደሆነ እና የቀረበበት ሪከርድ እን ደሌለ የሥራ ኃላፊነቱም የመዝገብ ቤት ሠራተኛ እንደነበረ የቤተሰብ ኃላፊ መሆኑ ታውቆ ቅጣት ይቀለልልኝ በማለት ጠይቋል::__

_የግል ተከራካሪዎቹ 7ኛው ተከሣሽም የቤተሰብ ኃላፊ መሆኑን በሕብረተሰቡ ዘንድ መል ካም ስም እንዳለውና ለዘሥም ሊከናወና ቸው መልካም ተግባራት ከተባበረት መንግሥታት በታማኝነት ለሰጠው አገልግሎት ማስረጃ የተሰጠው መሆኑን በመግለጽ ፍ/ቤት የወንጀሉ ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲቀለለት ጠይቋል::__

_የግል ተከራካሪ 8ኛው ተከሣሽም ይህ ወንጀል በተፈጸመበት ወቀት ዕድሜው አፍላ ወጣትና ተማሪ እንደነበረ በወቀቱ ንቃተ ሕሊናው ዉቂላ እንደነበረ ሟቾቹም ጓደኞቻቸው እንደ ነበሩ እና አሁን ግን በሁኔታው የተጸጸተ መሆኑን፣ ገልጾ ቅጣት እንዲቀልለት ጠይቋል::

_9ኛው ተከሣሽም ደካማ አባትና እናት ጧሮር የብዙ ቤተሰብ ኃላፊ መሆኑን የቀረበበት ሪከ ርድ እንደሌለና ይህንንም የወንጀል ድርጊት የፈጸመው በተማሪነት ዕድሜ ወቀት መሆኑን አሁ በመታሰሩ ምክንያት ቤተሰቦቹ በችግር ላይ መውደቃቸውን ገልጾ በወ/መ/ሕ/ቁ/79/1/ .ሀ፤ እና 184 መሠረት ቅጣት ቀሎ እንዲወሰንለት ጠይቋል::__

_11ኛው ተከሣሽ ይህ ድርጊት በሚፈጸምበት ወቀት 17 ዓመት ዕድሜ እንደነበረው እስከዛሬ ድረስ ሌላ ሪከርድ እንደሌለው ሙያውም በአሁኑ ወቀት ሀኪም እንደሆነ እና ለሕብረተሰቡ የሚጠቅመው ታሰር መቆሙ ሣይሆን ወጥቶ አገልግሎት ቢሰጥ የተሻለ መሆኑንና ፍ/ቤት እነ ዘሠን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ አስገብቶለት ቅጣቱን እንዲያቀልለት ጠይቋል::__

_12ኛው ተከሣሽም በዚያን ጊዜ ጨቅላ ወጣትና ምንም ሥልጣን ያልነበረው መሆኑን የቤተሰብ አስተዳዳሪ እና በመታሰሩ ምክንያት ቤተሰቦቹ በችግር ላይ የወደቁ መሆናቸውን ገልጾ ቅጣ ት እንዲቀለለት ጠይቋል::__

_13ኛው ተከሣሽም በዚያን ጊዜ በአስተማሪነት አዲስ ተቀጥር እዚያ መሄዱንና ስለአገባቡው ሁኔታ ስለማወቁን በሥራው ብዙ አገልግሎት መስጠቱን ሪከርድ እንደሌለበት ገልጾ በመታሰሩ ምክንያት ቤተሰቦቹ ለችግር መጋለጣቸውን ገልጾ ይህ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ገብቶለት ቅጣት እንዲቀለለት ጠይቋል::__

_ 14ኛው ተከሣሽ ይህ ድርጊት በተፈጸመበት ወቅት ለሁኔታው ወንጀል መሆን ምንም እንማያውቅ በወቅቱ ያለው ሁኔታ አስገድዶት መፈረሙን እሱ ራሱ በፀረ_አብዮተኝነት 7 አመት ታስሮ የነበረ መሆኑን በሥራው አገልግሎት የበጠ መሆኑን አሁን በዚህ ምክንያት በመታሰሩ ቤተሰቦቹ ለችግር የተጋለጡ መሆናቸውን ፣ ሣያውቅ በዚህ ጥፋት ውስጥ መግባቱን ገልጾ በእዚህ ምክንያት ቅጣቱ እንዲቀለለት ጠይቋል::__

_ከተከራካሪ ወገኖች የቀረበው የቅጣት አስተያየት መንፈስ በጥቅሉ ከዚህ በላይ በቅደም ተከተል የተዘረዘረው ሰመለስ ፍ/ቤቱም በሁለቱ ወገኖች ያቀረበውን የቅጣት ሀሣብና የሕጉን መንፈስ በማገናዘብ ቀጥሎ ያለውን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል::__

ን· ቀሣ ፎ· ቀ ፤

እነዚህም ተከሣሾች የተከሰሱት ወንጀል ድርጊት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለመፈጸማቸው ከቀረቡት የሰ ቁ 0/ሕግ የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች ተረጋግጠባቸው እንዲከላከሉ ፍ/ቤት መብታቸውን ቢሰቀላቸውም በዚህ መብት ተጠቅመው ለመከላከል ባለመፈለጋቸው ወይም መከላከል ባለመቻላቸው ለዚህ ለፈጸሙት ወንጀል ድርጊት ኃላፊና ተጠያቂ መሆናቸው ተረጋገጠ የጥፋተኝነት ውሣኔ ተሰጥቶባቸዋል::__

በወንጀሉ ውስጥ ላላቸውን ተካፋይነት ወይም የተሣትፎ ደረጃና መጠን በንመለከት በሕጉ አላማና መንፈስ መሠረት ከግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለበት ይታመናል::__

ስለሆነም ቅጣትን ለማቅለልና በማክበድ እነዚህ ተከሣሾች በዚህ በተፈጸመው ወንጀል ውስጥ ያላቸው ተሣትፎ ደረጃና መጠን በንመለከት በድርጊት አንድ ሥር ለተፈጸመው ወንጀል ጥፋተኞች ናቸው የተባሉት ተከሣሾች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዚህ ወንጀል ሥራ ተካፋይ በመሆን ራሣቸውን በኮሚቴ አዋቀረው አሠአፓ ናቸው በሚል ምክንያት ታስረው የነበሩት 8ቱ ወጣት ተማሪዎች አብዮታዊ እርምጃ ይወሰድባቸው በለው ወስነውባቸው ከተፈራረሙ በኋላ ከእሥር ከተለቀቁ ይጨርሱናል በሚል ሰበብ በወቅቱ የከ/ሀገሩ አስተዳዳሪ የነበረው ሻ/አ/ንጉሤ ፋንታን አስጠርተው ውሣኔአቸው ተግባራዊ እንዲሆን ጠይቀው እነዚያ ምስኪን ተማሪዎች ከታሰሩበት ወጥተው በጥይት እንዲረሸኑ ማስደረጋቸው የፈራጅን ሕሊና የሚሰቀጥጥ ከመሆኑም በላይ አሣዛኝም ነው::__

25ውን ክስ ወይም ድርጊት በንመለከት 8ኛው ተከሣሽ በ15ው ድርጊት ውስጥ የተጠቀሰውን ወንጀል ከፈጸመበት ዓመት በኋላ በ1976ዓ/ም ደህንነት መሰል ወንጀል ድርጊት

በመድገም ፀረ_አብዮትና ፣ ፀረ_ሕዝብ ወገቦቹ፣ የኦነግ አባላት ና ቸው በሚል ሰበብ በሌላ መዝገብ ከተከሰሱ ሌሎች ገራፊዎች ገብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን ሕዝብ በተሰበሰበበት እነ ምናለ መንገዴ የተባሉትን 8 ሰዎች እጃቸውን እና እግራቸውን አሥረው ኢ_ሰብዓዊ በሆነ መንገድ እንዲገደሉ ማድረጉ በጣሙን የሚያሳዝን ነው፡፡ __

3ኛውን ክስ በተመለከተ 6ኛው ተከሣሽ የ10 አለቃ ተሾመ ጉበና በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ከተወሰነው ገብረ አበሩ ሻ/ባሻ ፋንደን ሠፈራ ጋር በመሆን እነ አሰፋ ለገሠ የተባሉትን 7 ሰዎች ከሰር ጫካ ከድተው የወጡ ሚሊሺያዎች ና ቸው በሚልና በተለያዩ ምክንያቶች በመኪና ጭነው ከወሰዷቸው በኋላ አንድ ባንድ አውርደው ጨካኝ እና ነውረኛነትን በሚገልጽ ሁኔታ በጠመንጃ ደብድበው መግደሉ ለሰው ልጅ ውድ ሕይወት ምን ያህል ደንታቢስ መሆኑን ከድርጊት ሁኔታ በቀላሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡__

ስለሆነም እነዚህ ተከሳሾች በአጠቃላይ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ለፈጸሙት ወንጀል ሊወቀሱበትና ሊኮነኑበት የሚገባ ቢሆንም ለቅጣት መወሰን ያመች ዘንድ ከሕጉ አላማና ግብ አንፃር ቅጣትን ለማክበድ ወይም ለማቃለል አጥፊው የአለው የቀድሞ ሕይወት ታሪክ ምን እንደነበረ ለጥፋት ያነሳሱት ምክንያቶች ሁኔታዎች ምን እንደበረ አጥፊው በወቀቱ የነበረበት የኑሮ ሁኔታ እና የትምህርት ደረጃው የጥፋቱ ክብደትና የአፈጻጸሙ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ከወ/መ/ሕ/ቁ/86 ድንጋጌ በገለጸ ለመረዳት ይቻላል፡፡__

ይህንንም ጉዳይ ከዚህ አንጻር ስንመለከት እነዚህ ተከሣሾች ይህን ወንጀል እንፈጸሙ ያነሣሣቸው በወቅቱ የነበረው አምባገነናዊ መንግሥት ሕገወጥ አላማውን ከግብ ለማድረስ በተለያዩ ሕዝባዊ እና መንግሥታዊ ተቋማትን በማቋቋም ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሥርዓታቸው ተቃዋሚ የሆኑትን ወይም ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ የሚጠረጠራቸውን ኃይሎች ሀገሪቷ ያምታደደርበትን ሕግና ሥርዓት በተፃረረ መንገድ በመላ የሀገሪቷ ክፍሎች በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ይህ ሕገ ወጥ መዋቅር ከላይ አስከታች ዘርግቶ ለዚህ ሥርዓታቸው ፋገዝ ያልሆኑትን ዜጎች ሲያሰቃዩ መቆየታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡__

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዚያ ሥርዓት ውስጥ ተሣትፎውን ያላሳየ ዜጋ በጥርጣሬ አይን ስለሚታይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በአንዱ የመዋቅር ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ለሥርዓቱ ታማኝነቱን ለማሳየትና ለመኖር ሲል ሥርዓቱን ሲያገለግል መቆየቱ የግድ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡__

Mana Murtii Waliigalaa Oromiyaa

ስለሆነም በዚሁ ሥርዓት ውስጥ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ፣ ተፈጸሙት ወንጀሎች በወቅቱ ከዚሁ ሕገ ወጥ ሥርዓት የሚመነጩትን ፖሊሲዎች ያለምንም ማንገራገር ተቀብለው ተግባራዊ የሚያደርጉ የሥርዓቱ አስፈጻሚዎቹ ብቻ ሣይሆኑ ሥርዓቱ ራሱ ሊከሰስና ሊወገዝ የሚገባው ነው፡፡___

እነዚሁም ተከሣሾችም ከዚሁ በላይ በአጭሩ በተጠቀሱት ምክንያቶች በተለይ አብዛኞቻቸው የዚሁ ወንጀል ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ በእድሜ ያልበሰሉ ወጣት ተማሪዎች እንደነበሩ እና በወቅቱም የነበረት የሥርዓቱ ካድሬዎች በእነዚሁ ተማሪዎች የአፍላ እድሜ በመጠቀም ተማሪዎች ልባቸውና አላማቸው አንድ እንዳይሆን በአብዮተኛነትና በፀረ አብዮተኛነት ጎራ በመከፋፈል በሕገ_ወጥ ኮሚቴ ውስጥ መልምሎ በማስገባት በጓደኞቻቸው ላይ የማጋለጥ ዘመቻ እንዲያካሂዱ በማድረግ ከእነሱ መካከል ገራፊና አስገራፊን ፈጥሮ ለዚሁ ወንጀል መጠቀሚያ እንደ አደረጓቸው ፍ/ቤቱ ከሁኔታው ለመገንዘብ ችለዋል፡፡___

በሌላ በኩል ከእነዚሁ ተከሣሾች ውስጥ በሁለት የወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኞች ናቸው የተባሉት ተከሣሾችንም ሁኔታ ስንመለከት 6ኛው ተከሣሽ የ10 አለቃ ተሾመ ጉብና እና 8ኛው ተከሣሽ ሀብን አብዲ ሲሆኑ 6ኛው ተከሣሽ በወቅቱ በዚሁ ሥርዓት ውስጥ የነበረው ሥልጣን እንደሌለ እና ም/አ/ገዥ ፋንታ ሹሩር እንደነበር ከሌ ዐ/ሕግ ክስ ላይ ከመገለጹም በላይ እራሱም በሰጠው የቀጣት አስተያየት ላይ ከበላይ በተሰጠው ወታደራዊ ትዕዛዝ መሠረት ከመፈጸም ውጭ በራሱ ሥልጣን የፈጸመው ነገር እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ 8ኛውም ተከሣሽ ሙጀመሪያውን የወንጀል ድርጊት ሲፈጽም ከላይ እንደተገለጸው በእድሜ ያልበሰለ ወጣት ተማሪ እንደነበረና 2ኛውን ድርጊት የፈጸመው ሥራ ከያዘ በኋላ ቢሆንም ከበላይ በነበረበት ተፅእኖ እና ጫና ምክንያት ተገፋፍቶ የፈጸመው መሆኑ ስለተገነዘብን እንዲሁም 2ኛው ተከሣሽ አብዲሣ ደኑ 1ኛው የወንጀል ድርጊት ሲፈጽም የአውራጃ አስተዳዳሪ መሆኑ ቢገለጸም እሱም ከዚሁ በላይ ከተገለጸው ተፅዕኖ ውጭ ባለመሆኑ በአጠቃላይ እነዚሁ ተከሣሾች በሰጡት የቀጣት አስተያየት መሠረት በወቅቱ ከነበራቸው ዕድሜ እና የእውቀት ደረጃ አንጻር የሚፈጽሙት ድርጊት ውጤት ምን እንደሆነ ለይተው የማያውቁበት አፍላ እድሜ ላይ ነበረ ሌላ ሪከርድ ያልቀረበባቸው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ብዙ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች መሆናቸውና ካላቸው የትምህርት ደረጃ እና ሙያ አንጻር ለሀገርም ሆነ ለወገን የሚጠቅመው ታስሮ ከመቆየት በዚሁ ዕውቀትና ሙያቸው ተገቢውን አገልግሎታቸውን ቢሰጡ የሚመረጥ በመሆኑ ፣ የሕጉም ዋና አላማ አጥፊውን ቀጥቶ ለመበቀል ሣይሆን አስተምሮ

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa

../27

የጉዳዩን ሕብረተሰብ እንዳይከስና ወደ ሠላማዊ ኑሮው እንዳይመለስ ለማድረግ በመሆኑ እነዚሁን ሕጋዊ ገላጭ ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ እያገናኛቸው ደሏቸውን የተሳተፉ ደረጃና መጠን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ፣ ሁኔታውን በማጤን ፣_

1_6ኛው ተከሣሽ የ10 አለቃ ተሾመ ጉደና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ከግምት አስገብተን በወ/መ/ሕ/ቁ/79/1/ሀ/ እና 184 መሠረት ከተጠቀሰበት የሕግ አንቀጾች ሥር ከተደነገገው የቅጣት መነሻ በማውረድ በዚሁ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ዘታሰረበት ቀን ጀምሮ ታስቦለት ለዚሁ ለፈጸመው ወንጀል ለከሱም ሆነ ለሌሎች ትምህርትና ጥንቃቄ ይሆን ዘንድ በ20/ሃያ/አመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ፡፡_

2. 8ኛው ተከሣሽም ሀሰን አበጊ ለፈጸመው ተደጋጋሚ ወንጀሎች ከዚሁ በላይ በተገለጹት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እሱም በዚሁ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ታስሮ የቆየው ታስቦለት በ13 አመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ፣_

3ኛ 2ኛው ተከሣሽ አበጊሣ ደኑ በዚሁ ጉዳይ ተይዞ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ ታስቦለት በ8 አመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ በአንድ ወስነናል፡፡_

4. የተቀረት ተከሣሾች ¯ማለትም ፣

7ኛው ተከሣሽ በሉ ፈይሣ

9ኛው ተከሣሽ በንቲ ክሉ

11ኛው ተከሣሽ ደ/ር ረዳዒ ገምታ

12ኛው ተከሣሽ ደበሌ ዳባ

13ኛው ተከሣሽ ደ/ር ፈያሳ ቀና

14ኛው ተከሣሽ አንዳለ ሉተፋ

15ኛው ተከሣሽ ተሰፋዬ ተፈራ

18ኛው ተከሣሽ ዐርጌ ጉተታ

19ኛው ተከሣሽ ዓብንስ በለጠ

21ኛው ተከሣሽ አበማ ዑማና

23ኛው ተከሣሽ ተሰፋ ብርሃኑ

24ኛው ተከሣሽ ሙሰጠፋ አበጊሣ

26ኛው ተከሣሽ በቀለ ገመዳ እያንዳንዳቸው ከዚሁ በላይ እጃቸው ተይዞ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ ታስቦላቸው በ6 /ስድስት/ አመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ወስነን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡_

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa

**ት ዕ ዛ ዝ ፣**

በዚህ ውሣኔ መሠረት ተከታትሉ እንዲያስፈጽም ለጂማ ዞን ፓሀኒ ቤት ይጻፍ ብለናል:: በዚህ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን የይግባኝ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ብለናል::_

የዳኞች ፊርማ አለበት::

ዳኞች፣ መርጋ በካ

መሀመድ እስማዒል

ሌቲፓ ዐርጌሣ

ከሣሽ፣ የሌቀ ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም

ተከሣሾች፣ እነ ሻ/ል አበራ ጉበና አልቀረቡም::

መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ሉቀርብ የቻለው የጂማ ዞን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በቁጥር አስ/አስ/ፖ/58/92በ28/9/93 እና በቁጥር አስ/አስ/ፖ/58/92 በ28/9/93 በጻፈው ደብዳቤ 195ኛው ተከሣሽ ጫንስ በለጠ ፣ 245ኛ ተከሣሽ ሙሳጠፋ አብዲሣ ፣ 265ኛ ተከሣሽ በቀለ ገመዳ እና 235ኛ ተከሣሽ ተስፋ ብርሃኑ ፍ/ቤቱ እቀንዳንዳቸውን እጃቸው ከተያዘበት ቀን እንስቶ በ6/ስድስት/ አመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ብሎ ወስኖ ነበረ ይሁን እንጂ ፍርደኞቹ ከተወሰነባቸው እስራት ውስጥ 2/3ኛ /ሁለት ስስተኛውን የፈጸሙ እንደሆኑ እና 1/3ኛበኮሚቴ ታይቶ መውጣት ያለባቸው መሆኑን ስለተወሰነ በአመክሮ ሕግ 207.ሀ.ለ.ሐ.እና 208 .ሀ.ለ መሠረት እንዲፈቱ ብሉ ስለጠየቀ ነው::__

**ት ዕ ዛ ዟ ዝ ፣**

ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት ፍርደኞች 1. ጫንስ በለጠ ፣ 2. ሙሳጠፋ አብዲሣ፣ 3. በቀለ ገመዳ ፣ 4. ተስፋ ብርሃኑ ከተወሰነባቸው 6 አመት ውስጥ 2/3ኛውን /4 አመት /ስለታሰሩ እና 1/3ኛ/2አመት/ በአመክሮ ስለቀረ ወሀኒ ቤት በጠየቀው መሠረት ለተከሣሾች በወሀኒ ቤት በኩል አስፈላጊው ምክር ከተሰጣቸው በኋላ እንዲለቀቁ ታዟል ይጻፍ::

....29

ዳኞች፡ ወርጋ ቦካ
መሀመድ ኢስማዔል
ኡጉቻ ዐርጌሣ

ከሣሽ፡ ል ዩ ዐ/ሕግ አልቀረበም

ተከሣሾች፡ እነ ሸ/ል አበራ ጉበና አልተቀረቡም::

ይህ መዝገብ ተወስና ከተመለሰ በኋላ ከመ/ቤት ሊቀርብ የቻለው የደማ ዞን ማረሚያ ቤት በቁጥር እስ/እስ/5/58/92 በ28/9/93 በጻፋቸው የአመክሮ ፍርዎች ፤

1. ተስፋዬ ተፈራ የተከሰሰው የሕግ እሥረኛ የአመክሮ ጊዜ ታስቦለት በ14/01/949/ም የሚፈታ፤
2. ዳ/ር ፈቃዱ ፍኖ የተባለው የሕግ እስረኛ የአመክሮ ጊዜ ታስቦለት በ16/1/94 ዓ/ም የሚፈታ መሆኑን፤
3. ደበሉ ዓባ የተባለው የሕግ እሥረኛ የአመክሮው ጊዜ ታስቦለት በ15/01/94 የሚፈታ መሆኑን፤
4. በንቲ ቦሉ የተባለው የሕግ እሥረኛ የአመክሮ ጊዜ ታስቦለት በ2/1/949/ም የሚፈታ መሆኑን ፤
5. ዐርጌ ጉተታ የተባለችው የሕግ እሥረኛ የአመክሮ ጊዜ ታስቦላት በ22/1/94 የምትፈታ መሆኑን፤
6. በሱ ፈይሣ እና እንዳለ ኢተፋ የተባሉት የሕግ እስረኞችን በማመልከት በቁጥር እስ.እስ/15/58/93 በ06/10/939/ም በተጻፈ አመክሮ ጊዜ ታስቦላቸው በ03/2/94 የሚፈቱ መሆናቸውን በመግለጽ በወ/መ/ሕ/ቁ/በ2፤ 2067 207፤ እና 208 መሠረት እንዲፈቱ በመጠየቁ ነው::

227

ት ዕ ዛ ዝ ፤

ነዚሁ ስማቸው ከዚሁ በላይ የተዘረዘረው የሕግ እስረኞች እንዲታሰሩ ከተወሰነባቸው ጊዜ ውስጥ በሕጉ መሠረት በአመክሮ ለመፈታት የተፈቀደው ጊዜ ታስቦላቸው የሚፈቱት በ19949/ም መሆኑንና ይህ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ወህኒ ቤት [illegible] እነዚህን እስረኞች እንዲፈቱ ጥያቄ ማቅረብ [illegible] የዚሁ ችሎት የቀጠሮ አጀንዳ ከጥቅምት 12/949/ም ጀምሮ በመሆኑ ከወህኒ ቤት በቀረበው ጥያቄ መሠረት ደንቡ እነዚሁ የሕግ እሥረኞች ከዚሁ

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa
መዝገብ ቤት
የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት

5../30

ቾሎት መደበኛ ቁጥር በፊት የአሥራት ግዜያቸው የሚያለ መሆኑን ስለተገነዘበን ከጀማ ወሀኒ ቤት በቀረበው መረጃ መሠረት ፤_

1_ የሕግ እሥረኛ ተበፋ ፄ ተፈራ በ14/1/949/ም

2_ የሕግ እስረኛ ደ/ር ፈያሳ ኛ በ16/1/949/ም

3_ የሕግ እሥረኛ ደበሌ ዓባ በ15/1/949/ም

4_ የሕግ እስረኛ በንቴ ከሚ በ2/1/949/ም

5_ የሕግ እስረኛ ዐርጌ ጉተታ በ22/1/94

6_ የሕግ እስረኛ ከሌ ፈደሣ በ3/2/949/ም

7_ የሕግ እስረኛ አንዓለ ሎተፋ በ3/2/94 9/ም የሚፈታ መሆኑ ስለተረጋገጠ ለን እነዚህ የጀማ ታራሚያቾ በዚሁ በላይ የተጠቀሰው የቅጣቻ ግዜያቸው ሲደርስ የተ መሰከረው ወሀኒ ቤት እንዲለቃቸው ይሁን:: በለን መዝገቡን መለስናለ::__

የዳኞቾ ፊርማ አለበት::

<u>ተ ጨ ማ ሪ ት ዕ ዛ ዝ፤</u>

የሕግ ታራሚያቾ አበዲሣ ደቱ እና አቦማ አመና በ22/9/93 በ22//09/ 9 3 እና በ24/9/93 በጻፈት ማመልከቻ የተወሰነላቸውን የአሥራት ግዜያቸውን በጊምቢ እና በምሥራቅ ወለጋ ማረሚያ ቤት እንዲጨርሱ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ስለጠየቁ የወሀኒ ቤት ደንበኛ መወሪያ በሚፈቅደው መሠረት በራሣቸው ወጭ ተወስደው በጠየቁት ወሀኒ ቤቶቾ አማካኝነት ቀሪውን የአሥራት ግዜቶቸውን እንዲጨርሱ እንዲደረግ ይሁን በለናል::__

የዳኞቾ ፊርማ ፤ አለበት::

Mana Murtii Waliigala Oromiyaa